No 20

# Radio Rainbow
## ቀስተ ደመና ሬዲዮ
## Radio Arc - En - Ciel


C/o P.O.Box 140 104. 53056 BONN. GERMANY - Fax: (49) 228 / 61 23 81

ቀን / Date 12-02-91

**የፓሪሱ ጥሪ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረበ የትግል ጥሪ እንጂ ለወያኔ የተላከ የልመና ማመልከቻ አይደለም።!!**

ዛሬ ይሁን የዛሬ አሥርም ሆነ ሃያ ዓምት የሐገራችን ችግሮች የሚፈቱት በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ አመቺ የሆነ የሃይል ሚዛን ተፈጥሮ በዚህ የሃይል ሚዛንና በሱ አማካይነት ብቻ የሕብረተሰቡን ትክክለኛ ፍላጎት በሚያንጸባርቅ ሁኔታ ነፃ ምርጫ ሲካሄድ ነው። ይህንን የነፃ ምርጫ ቅድመ ሁኔታ የሆነ ለዴሞክራሲ የሚያመች የኃይል ሚዛን ለመፍጠር ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ተቃዋሚ ኃይሎች በጋራ መታገል እንዳለባቸው ከየአቅጣጫው በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ፓሪስ የተገኘውን ድል ታሪካዊ የሚያደርገው በዚህ በዴሞክራሲ ጥያቄና በነፃ ምርጫ ጉዳይ ስምንት ድርጅቶች አንድ የጋራ ሰነድ ላይ መስማማታቸውና በዚህም የጋራ አማራጭ ሰነድ አማካይነት በሕብረት ለመታገል መወሰናቸው ነው።

የኢተፖድህ የነፃ ምርጫና የብሔራዊ ውይይት ጥሪ የኢትዮጵያ ሕዝብና ታጋይ ልጆቿ በዚህ አማራጭ ዙሪያ ተሰብስበውና ተደራጅተው ወያኔ/ኢህአዴግን አስጨንቀው እንዲይዙ የቀረበ የትግል ጥሪ እንጂ፤ ለዚህ ጸረ ሕዝብና ፀረ ደሞክራሲ ሃይል የተላከ የልመና ማመልከቻ አይደለም። የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ዛሬ በጋራ እየተያያዙት ያለውን አዲስ የትግል ምዕራፍ ሲጀምሩ፤ ይህንን መሠረታዊ ሃቅ በትክክል ካልተረዱ ከፍተኛ ውዥንብር ውስጥ የሚወድቁበትና ትግላቸውም መልሶ የሚሽመደመድበት አዘቅት ውስጥ እንደሚወድቁ ከወዲሁ ለመተንበይ ምንም አስቸጋሪ አይሆንም። የኢተፖድሕን የትግል ዓላማና ሂደት በትክክል ከተረዱት ግን የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች ለሚጠብቃቸው ረዥምና ውስብስብ ትግል አስፈላጊ የሆነውን ጥራት ተላብሰዋልና ለየምዕራፉ አስፈላጊ የሆነውን የትግል ስልትና ዕቅድ በሥራ ላይ እያዋሉ ትግሉ ወደፊት እንደሚራመድ የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው።

የኢተፖድህ ጥሪ የትግል ጥሪ እንጂ የልምና ማመልከቻ ባለመሆኑ፤ የፓሪሱ ጥንስስ ስኬታማነትም ሆነ ውድቀት ዞሮ ዞሮ የሚለካው ወያኔ/ኢህአዴግ ዛሬ ለብሔራዊ ውይይት ጥሪ በሚሰጠው አወንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ወይም ደግሞ ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ለተደረገው ጥሪ የዛሬ ዓመት ተኩል በሚሰጠው አወንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ ብቻ አይደለም። የትግል ጥሪ በመሆኑ ስኬታማነቱ የሚለካው ጥሪው የተላለፈላቸውን ኢትዮጵያውያን ሁሉ፤ ከኢትዮጵያ ከራሷ ተነስተው እስከ ሰሜን አሜሪካ፤ ከአውሮፓና አፍሪካ እስከ እስያና አውስትራልያ ለማንቀሳቀስና ለማደራጀት የኢተፖድህ አባላት፤ ሌሎች አገር ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን በሚያሳዩት ታታሪነትና ይህ ትግላቸው በሚሰጠው ፍሬ ነው።

ኢተፖድህና ደጋፊዎቹ አገር ወዳዶችና ዴሞክራቶች ዛሬ ሳይውሉ ሳያድሩ፤ ዛሬ የፓሪሱ ጥንስስ ቅስም ሳይሰበር ተሟሙተው የትግሉ ጥሪ ከቀረበላት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሃል በሺ የሚቆጠሩ ዜጎችን በድጋፍ ኮሚቴዎችም ሆኑ ሌሎች ስብስቦች ካንቀሳቀሱ ነገ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ለቀጣዩ ትግል ከጎናቸው ያሰልፋሉ። በዲፕሎማሲውም መስክ እንደዚሁ ዛሬ በኢተፖድህ ግልጽና ዴሞክራሲያዊ ጥሪ ዙሪያ የሚሰበስቡት ድጋፍ ለቀጣዩ ትግል የዚያኑ ያህል አመች ሁኔታን መፍጠሩ የሚያጠራጥር አይደለም። በመሆኑም በመጭዎቹ ወራት የኢተፖድሕና የደጋፊዎቹ

ርብርቦሽና ጭንቀት የአገራችን እድል በእሱ እጅ ውስጥ ያለ ይመስል "ወያኔ/ኢህአዴግ ምን መልስ ይሰጥ ይሆን?" ይሰጥ ይሆን እያሉ ነገሩን ሁሉ እዚህ ጥያቄ ላይ ማንጠልጠል ሳይሆን፤ በፓሪሱ ሰነድ አማካይነት የትግል ጥሪ የቀረ ላቸውን ኢትዮጵያውያን ወንድሞችና እህቶች በየአሕጉሩና በየአገሩ በተለያዩ ደረጃዎች ለማሰባሰብና ለማደራጀት መሆን ይገባዋል እንላለን።

በዚህ መልክ ፊታቸውን ወደዋናው ባለጉዳይ ወደኢትዮጵያ ሕዝብና ወደታጋይ ልጆቿ አዙረው ከሠሩ ወያኔ/ኢሕአዴግ ዛሬ የብሔራዊ ውይይቱን ጥሪ አሻፈረኝ ቢል፤ የዛሬ ዓመት ተኩል ደግሞ የፓሪሱ ሰነድ ስለነፃ ምርጫ ያስፈራቸው ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች ሳይሟሉ በቅድሚያ የወንበር ፍርፋሪ ተቋርጠው በሥነሥርዓት አድማቂነት ከሚያገበድዱለት አንዳንድ ተቃዋሚ ተብየዎች ጋር ተመሳጥሮ የሸፍጥ ምርጫ ሂደቱን ቢቀጥል፤ ከወዲሁ ለቀጣዩ ትግል ሁኔታዎችን አመቻችተዋልና ወያኔ ከዚህ ሂደት ተጳክሞ እንጂ ተጠናክሮ አይወጣም። በውስጡ ያለው ቅራኔና ክፍፍል ያድጋል እንጂ አይጠብም። ዴሞክራቶች ባደረጉት ጥረት ሕዝቡ ግልጽ አላማና የትግል መፈክር ይዟልና ወያኔ በዚህ በአሻፈረኝ ባይነቱና በምርጫው ፈዙ ይበልጥ ይጋለጣል እንጂ ሻማ ያገርዎችም በምርጫ ተብየው ስለተደባለቁት ብቻ ይበልጥ ሕዝባዊ ቅባሎት አያገኙም። በዴሞክራሲያዊ ተቃዋሚ ሃይሎች ሰፈር ደግሞ ከወዲሁ ግልጽ በሆነ ዴሞክራሲያዊ ሰነድ ዙሪያ ከዕለት ዕለት እየተደራጁና እየጳበረ የሚሄድ ትግል ስር ሰዷልና የወያኔም አሻፈረኝ ባይነት ፓሪስ ተሰብስበው ለነበሩ ሰላሳ የድርጅት ተወካዮች የተሰጠ አሉታዊ ምላሽ ብቻ ሳይሆን፤ የሕዝብን ጩኸት ከመጤፍ የማይቆጥር እብሪተኛ መሆኑ ተረጋግጧልና ለቀጣዩ ትግል ጥራትን እንጂ ውዥንብርን የማያውቅ አመቺ መድረክ ይፈጠራል ማለት ነው።

ነገሩ እንደዚህ ግልጽ ከሆነ ዘንድ ለኢተፖድህና ለትግሉ ሥረ መሰደድ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ አሳሳች አቅጣጫዎችን በእንጭጫቸው ማጋለጥ አስፈላጊ ነው እንላለን።

በአንድ በኩል ወያኔ/ኢህአዴግ የለየለት ፀረ ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ ሃይል በመሆኑ ከሱ በልመና የሚገኝ ምንም ነገር ስለሌለ ጊዜ አናጥፋ የሚሉ አሉ። እንደዚህ ዓይነቱን የሚነዙ ዜጎች የፓሪሱ ጥንስስ ያልገባቸው ወይም እንዲገባቸው የማይፈልጉ ዜጎች ናቸው። መጀመሪያ ኢትፖድህ በእነዚህ ሰነዶች አማካይነት ታግሎ ያታግል ተባለ እንጂ ወያኔን ይለምን፤ ዲፕሎማቶችን ይማጸን ያለ ማንም የለም። ሁለተኛ የአስተሳሰባቸው ቅራኔ አልታያቸውም እንጂ እንዲያውም በየትኛውም የትግል ስልት ቢሆን ከልመናና ከውድቀት የምንወጣው በግልጽ ሰነድ ዙሪያ ሕዝብን አደራጅቶ በማታገል እንጂ የቅስቀሳውንና፤ የማደራጀቱን ቅስም በሆነ ባልሆነው ሰበብ በመስበር አይደለም።

በሌላ በኩል ደግሞ የፓሪሱ ሂደት ቅስም እንዲሰበርና በፓሪሱ ሕብረት ስብርባሪና ላይና መልሶ ውዥንብርና ተስፋ መቁረጥ ባሕር ውስጥ በተዘፈቀ የተቃዋሚዎች ሰፈር የተሻለና የጠነከረ ሕብረት የሚሳካ የሚመስላቸው ሃይሎች ሊኖሩ ይችላሉ። በሐገሪቱ አሉ ከሚባሉት ዋና ዋና ተቃዋሚ ድርጅቶች ስምንቱ በጋራ ሰነድ ዙሪያ የተሰባሰቡት፤ የሕዝብ ድጋፍ ከዳር እስከዳር የተንጸባረቀበት፤ የታጋዮች ሞራል ከአለፉት ዓመታት እጅግ ከፍ ያለበትና በዲፕሎማሲያዊውም መስክ መልካም ጅማሮ እየተባለ ድጋፍ እየተሰበሰበ በሚኬድበት ሁኔታ ውስጥ እያለን ባይሆን የጎደለውን እያሟሉ በዚህ ላይ መገንባት ሲገባ ትኩረትን ማሰበጣጠር እጅግ አደገኛ ስሌት ነው። ውጤቱም ማለቂያው ለማይታየን ረዥም ጊዜ በስንት ድካም ተመልሶ የተገኘውን የዲፕሎማሲና የፖለቲካ አጥቂነት ሰዶ እንደገና ማሳደድ ስለሚሆን፤ እጅግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ቀስተ ደመና ሬዲዮ
22/10/98